# አዳም በገጸ-ባህሪያቱ ለምን ይወቀሳል?

*Teshale Kebede Bedriya*

"በነገራችን ላይ አዳሙ ስለተባለ አውቃለሁ ባይ፣ ድራሽ ቢስ የዘመኑ ደብተራ ላወራ አልፈልግም" (የስንብት ቀለማት፣165)

የድህረዘመናዊነት (Postmodernism) ማዕከላዊ ዕሳቤ የሚያርፈው ተፈጥሮአዊ አድርገን የተቀበልናቸው ገናን እውቀቶችን፣ እሳቤዎችን፣ ብያኔዎችን…ተፈጥሮአዊ እንዳልሆኑ በማሳየት ነው ትላለች፤ Linda Hutcheon፣ 'The Politics of Postmodernism' በተሰኘው መጽሃፏ፡፡The postmodern initial concern is to de-naturalize some of the dominant features of our way of life...

እነዚህን ገናን ብያኔዎችና የሕይወት ዘይቤዎች የባህል ስሪት (social construction) በመሆናቸው ነው፤ እንደተፈጥሮአዊ፣ የማይለወጡና ዘላለማዊ እውነት አድርገን እንዳንወሳደቸው አሳብያኑ የሚያሳስቡን፡፡

አዳምም ልክ እንደ ድህረዘመናዊ ከያኒያን ሥነጽሁፋችን ውስጥ ቀኖናዊ የሚመስሉ ልማዶችና ብያኔዎችን በመሻር አዳዲስ ስልቶችን በድርሰቶቹ ውስጥ አስተዋውቋናል፡፡ ይኼ ማለት ግን አዳም የድህረዘመናዊነት እሳቤ አራማጅ ወይም አቀንቃኝ ደራሲ ነው ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን የድህረዘመናዊነት እሳቤዎችና ቴክኒኮችን በጥንቃቄ እየወሰደ በድርሰቶቹ ውስጥ በስፋት ይጠቀማል፡፡

በሃገራችን ያልተሞከሩ የአከያየን ዘይቤዎችን ሞክሮ የተሳካለትም ጥንቁቅ አንባቢና ያነበበውን አውዳዊ አድርጎ በማምጣት የተካነ ደራሲ በመሆኑ ነው፡፡ በድህረዘመናዊ ልብወለዶች ውስጥ እንደሚስተዋለው፣ አዳም የገጸ-ባህርያቱ ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን ራሱን እንደአንድ ገጸባህሪ አድርጎ በ'የስንብት ቀለማት' ውስጥ ሚና ወስዶ ተጫወቷል፡፡ ተጫውቶም ተሳክቶለታል፡፡

አዳም በዚህ ልብወለዱ ውስጥ መንታ ማንነትን ተላብሶ ሲተውን እናገኘዋለን፡፡ በደራሲነቱ የምናውቀው አዳምና አስረግዞ የጠፋው… አዳ(ሙ)ም፡፡ በሁለቱም ማንነቱ ገጸ-ባህሪያቱ አጥብቀው ይነቅፉታል፣ ያንጓጥጡታል፣ ያሙታል፡፡

ያቺ ሰዎችን በሴራና በተንኮል ጠልፎ መጣል 'ሆቢዋ' የሆነው በ'የስንብት ቀለማት' ውስጥ የምንተዋወቃት ሳላይሽ ምናልባት የምታፈቅረው አዳሙ የተባለ "የዘመኑ ደብተራ" ጥሏት ስለሄደ ይሆን? ባህሪዋ የከፋው! ማን ያውቃል?...

እስኪ ከሳላይሽ አንደበት፤ "ከለይኩን ጋር ከተቀራረብን በሁዋላ አንድ ቀን በጨዋታ መሃል ባልጠበቅሁት ጊዜ የአዳሙ ወዳጅ ('ወዳጅ' የሚለው ቃል አያስቅም? በነገራችን ላይ አዳሙ ስለተባለ አውቃለሁ ባይ፣ ድራሽ ቢስ የዘመኑ ደብተራ ላወራ አልፈልግም) አልነበርሽም እንዴ? አለኝ ሳቅ እያለ፡፡ ምናልባት ስለአንቺ ሁሉን ነገር አውቃለሁ ሊለኝ እንደሆነ ይገባኛል፡፡

"እንዴት አወቅህ አንተዬ? ምናምን አልኩት የተገረመ መስዬ፡፡…

"'በደንብ አውቅሻለሁ' ሲለኝ የቅርብ ጓደኛዬ ኀብስት አዲስአባ ኤዞፐ የተባለ አንድ የግሪክ መድሃኒት ቤት እንደምትሰራ፣…ወዳጇ የነበረው ደራሲ አዳም (የብዕር ስሙ ነው፣ ሌላ ስም ጠፋ እንዴ?) በጥጋብ አገሩን ከድቶ እንደሸሸ፣ ብቻ ሌላም ሌላም የረባ ያልረባውን ዘርዝሮ ነገረኝ፡፡"

አዳም ዲሞክራት ደራሲ ነው፡፡ የመለመላቸው ገጸ-ባህሪያት ሚና-ሚናቸው ሰጥቷቸው ሲጫወቱ ከላይ ሆኖ መመልከትን አልፈቀደም፡፡ እሱም የእነሱ አካል ሆኖ ቀረበ እንጂ፡፡ ለነገሩ ሁሉም ነገር ታስቦና ታቅዶ የተዋቀረና የተሰራ ነው ካልን፣ እኛም በሆነ መንገድ ገጸ-ባህሪ ነን፤የሆነ ሚና ተሰጥቶን የምንጫወት፡፡ ስለዚህ እውንና ቅዠት የሚሉ ዳይኮቶሚዎች ብዙም አያስኬዱንም፡፡

"ሰሸን ዶርስ ሁለት ቀን አደርኩ፡፡ ከማን ጋር መሰለህ የተደበቅነው ከአዳሙ ጋር፡፡ የሚያውቃት ልጅ ነበረች እዛ የምትሰራ ስሟ ጠፋኝ የሆነ የወፍ ሥም ነገር [የቹቹ እናት ላስታ ነች]፡፡…

አዳሙ አለ እባክህ? አራት ኪሎና ስድስት ኪሎ አካባቢ ከአንድ ሚጢጢ ቀይ ልጅ ጋር [ሳላይሽ] አንዳንዴ አየው ነበር፡፡

ሆላንድ ተተከለ አይደለ እንዴ?

ሆላንድ ሄደ? ፎጋሪ ነበር አቦ፡፡ ለምን? ለትምህርት ወይስ አቀጣጠነ? አንዳንዱ ድምጹን እያጠፋ ይሰወራል፡፡" (ስ.ቀ፣319)

አዳም በዚህ ውድ ልብወለዱ ውስጥ ፍዝ ገጸ-ባህሪ ሆኖ ነው የተከሰተው፡፡ ሌሎች ገጸ-ባህሪያት ናቸው ስለሱ የሚነግሩን፡፡ በገጸ-ባህሪያቱ ስለአዳም የሚተረክልን አንዳንድ ነገሮች ግነት አያጣቸውም፡፡ እንደቹቹ ያለች ሴት የምታቀርበው ወቀሳ ግን ቸል የሚባል አይደለም፡፡

በሚያምረው 'ኮልታፋ' አንደበቷ ቹቹ ትናገራለች፤ "እማ አፍ አውጥታ 'እኔ እናትሽ ሸልሙጣ ነኝ ብላኝ አታውቅም፡፡ ኩላቷ ያሳዝናል፡፡…አባት የለኝም፣ ማለቴ አባቴን አላውከውም፡፡ ካላሳደገኝ 'አለኝ ማለት እችላለሁ? ድልክና ይሆናል አይደለ?...በክልብ ደሞ አባትሽ 'አዳሙ' ይባላል እና ልጅ ከእኔ እንደወለደ አያውክም፡፡ አሁን የት እንዳለ እንጃ አለችኝ፡፡ እማ ሃያ አይሞላትም ስትወልደኝ…ይገልምሻል እስከዛሬ አዳሙን ትወደዋለች፡፡አምልጧት ስትምል 'አድዬ ድለስ' ትላለች፡፡ሺት ነች አይደለ፡፡እንደዛ ስትል ይደብለኛል፡፡ ማነው ይሄ ደግሞ አድዬ? ምናምን እላታለሁ፡፡'ዝምበይ' ትለኛለች፡፡…ሃንድለድ ፐልሰንት እልግጠኛ ነኝ ከሴተኛ አዳሊ በመውለዱ ነው የጠፋው" (ስ.ቀ፣387)

አንድ ማሳያ ላክል፤በ'የስንብት ቀለማት' ውስጥ በገጣሚነቱና በሰዓሊነቱ የሚታወቀው የወርቁ ዕንቁባህርይ ስራዎች ከአዳም ረታ ስራዎች ጋር ይመሳሰላሉ በሚል ለሚቀርበው 'ትችት' ዮሃንስ ወላይሶ የተባለ የባህል ሃያሲ የሰነዘረውን ትችት እንመልከት፡፡ "በስራ ውጤታቸው ብቻ ሳይሆን (ዱካው ቀርቶ) በከያኒነት ማንነታቸው ወርቁና አዳም ይለያያሉ፡፡ ደራሲ አዳም በአሁን ጊዜ ሆላንድ ይኖራል ሲባል ሰምቻለሁ፡፡

በስደት ይሁን በጥጋብ፣ በስራ ይሁን በልመና አይገባኝም፡፡ እንዴት ደራሲ እዛ አውሮፓ እየኖረ ስለዚህ አገር ወጣ ገባ ይጽፋል?...ከሃገሩ ለምን ይሸሻል? በሸሸቱ ምን ሊያገኝ? ካላገኘ ደግሞ ምን ሊፈጥር?"

በነገራችን ላይ የአዳም የልጅነት ስም አጠራሩ "አዳሙ" ነው፡፡ በአዳምና በአዳሙ፤ በደራሲው አዳምና በንፋስ ስልክ ወዳጆቹ በተደጋጋሚ ስሙ በሚነሳው አዳም መካከል የተሰመረው መስመር ገጥሞ ይቀላቀላል፡፡

ልክ እንደዚሁ በምናብ የተፈጠረችው የሻገር ሆቴል ባለቤቷ በትግስት (ቲጊ) እና በወዳጅዋ በታዋቂው ሙዚቀኛ ካሳ ተሰማ መካከል የተሰመረው መስመር ሲደበዝዝ በልብወለዱ ውስጥ እንደምናነበው፡፡ ለዚህ ነው 'እውናዊ የትኛው ነው?'፣ 'ምናባዊውስ ? '...የሚለው በልብወለዱ ውስጥ የሚምታታብን፡፡ መግቢያዬ ላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በድህረዘመናውያኑ እሳቤ ውስጥ እውናዊና ምናባዊ፤ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ የሚባሉ ወሰኖች ይፈርሳሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ እያንዳንዳችን "እኔ" ወይም "ሰው" ብለን የያዝነው አረዳድና ግንዛቤ ሳይቀር ማህበረሰብ ሰራሽ እንጂ ተፈጥሮአዊ አይደሉም፡፡ በዚህም እውኑ ልብወለዳዊ፣ ልብወለዳዊው ደግሞ እውናዊ ሊሆን ይችላል፡፡

ፈረንሳያዊ ፈላስፋ Gilles Deleuze የኪነት (ሥነጽሁፍን ጨምሮ ሌሎች ምናባዊ የፈጠራ ሥራዎች) ዋነኛ ተግባር ማስተማሰልና የወል የሕይወት ልምድ ወይም ዘይቤ ማስተጋባት አይደለም ይለናል፡፡ ከዚያ ይልቅ ተቀብለነው የምንኖረው የሕይወት ልማድና ብያኔ በሃሳብ መነቅነቅ ነው የኪነት ተግባር፡፡ ከዚህ ከተነቀነቀው ወይም እንዲታወክ ከተደረገው ልማድ ውስጥ ከያኒው ሌላ አይነት የሕይወት መንገድ እንዳለ የማሳየት፣ አማራጭ ዓለማትን የመስራት ግዴታ ይወድቅበታል፡፡ "Literature would not be based on representing or expressing some common worldview or shared experience; literature Should shock, shatter and provoke experience."

አዳምም በድርሰቶቹ ውስጥ አዳዲስ የሕይወት መንገዶችን በመቀየስ፣ ለሃገራችን እንግዳ የሆኑ አዳዲስ ስልቶችን በማስተዋወቅ፣ ከምንም በላይ ደግሞ ከዚህ ለዛዛና ድግግሞሻዊ ዓለም አውጥቶ በፈጠራቸው ኪናዊ ዓለማትን ውስጥ ገብተን እንድንደሰት ማድረግ ችሏል፡፡ ለዚህ እኮ ነው አዳም ኹነኛ ደራሲና ፈላስፋ ነው የምለው !